Seattle Public Utilities

ጥሩ ነገር ለምን ይበላሽ?

ምግብና የጓሮ ጥራጊ

እነዚህን ነገሮች በምግብና የጓሮ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ያስቀምጡ

የምግብ ፍርፋሪዎች

ፍራፍሬዎች

ቅጠላቅጠሎች

የተፈጨ ቡናና ማጥለያው

የሻይ ኮሮጆዎች

ግልፋፊና አጥንት

ፓስታና ሩዝ


የእንቁላል ቅፋፊ ፡ የኦቸሎኒ ዓይነት ግልፋፊ

ዳቦና ጥራጥሬዎች

ሥጋ ፡ ዓሣ እና የወተት ውጤቶች

ምግብ-የነካካው ወረቀት

የወረቀት ኮሮጆዎች ፡ የወረቀት ፎጣና ናፕኪን

ቅባት የነካካው የፒዛ መያዣ ቀፎ

ያልተቀባ ምግብ-የነካካው ወረቀት

የተቆራረጠ ወረቀት
(ከጓሮ ጥራጊ ጋር ይደባለቅ)

ተክል እና የጓሮ ጥራጊ

አበባዎች እና የቤት ተክሎች

ቅጠሎች ፡ ቅርንጫፎች እና የሣር ቁርጥራጮች

ፕላስቲክ ፡ ጠርሙስ ወይም ብረታብረት አይሆንም

የምግብ ትርፍራፊን ለምን እንሰበስባለን?

ጥራጊን ለመቀነስ ፡ ከሲያትል መኖሪያ ቤቶች ቆሻሻ አንድ-ሦስተኛው እጅ የምግብ ጥራጊ ነው። ወደ መሬት መሙያ ጉድጓድ ከመጣል ይልቅ በአካባቢ የሚገኝ የመናፈሻ ቦታዎችና የአታክልት ቦታዎች አፈርን ለማዳበር ወደ ኮምፖስት መቀየር።

የተፈጥሮ አካባቢ ፡ በመሬት ጉድጓድ መሙያ ውስጥ የምግብ ጥራጊ ሜቴይን የሚባል ጋዝ ይፈጥራል - የግሪንሃውስ ጋዝ ሲሆን ከ ጨ2 22 ጊዜ የበለጠ በጣም አደገኛ ነው። በቅርጫቱ ውስጥ በማጠራቀም የአየር ንብረትን ይጠብቁ።

ወጪው ፡ ውድ የሆኑ የጥገናና የተደፈኑ ቱቦዎችን መከፈቻ ወጪዎችን ያድኑ። የምግብ ትርፍራፊዎችን ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ከማጠራቀም በምግብ ትርፍራፊ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ያከማቹ። ይህም ውሃንና የኃይል ምንጭንም ይቆጥባልእ

በቅርጫት ውስጥ ምን መግባት ስላለበት ጥያቄዎች አሉዎት?

ለጋርደን ሆትላየን (የነፃ ስልክ መስመር) ይደውሉ

(206) 633-0224

ወይም

www.seattle.gov/util/foodwaste

ስለ ማዕድቤት መጠቀሚያ ሃሳቦች በሌላው ገጽ ይገኛሉ ▶

ለአፓርተማዎችና ኮን ሚኒየም

የመጋዘን መጠቀሚያ ሃሳቦች

ጥሩ ነገር ለምን ይበላሽ?

ከ140,000 በላይ የሚሆኑ የሲያትል ቤተሰቦችና በመቶ የሚቆጠሩ ባሉ-ብዙ ቤተሰብ ቤቶች የምግብና የጓሮ ጥራጊ ስብሰባ አገልግሎት አላቸው። የምግብና የጓሮ ጥራጊ ቅርጫቶች ውስጥ በየሳምንቱ የተጠራቀመው ይሰበሰባል። የማዕድቤት ትርፍራፊን ለመሰብሰብ ቀላል እንዲሆን ለመርዳት የሲያትል ነዋሪዎች ያካፈሉን ጥቆማ ሃሳቦች እኚሁና ፡

በኮሮጆ ውስጥ ያስቀምጡት

ቡናማ መልክ ያለውን የወረቀት ኮሮጆ ወይም የተፈቀደ ከሱቅ የምግብ መያዣ ኮሮጆን የምግብ ትርፍራፊን ለማጠራቀም ይጠቀሙ። ሙሉውን ኮሮጆ የምግብና የጓሮ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ያከማቹ። ስለሚፈቀዱ ወደ አፈር-ተለዋጭ ኮሮጆዎች ለማወቅ Visit **www.seattle.gov/util/foodwaste** ይጎብኙ። በዝርዝሩ ላይ ካላዩት - አይጠቀሙበት!

የፕላስቲክ ኮሮጆዎች በቅርጫቱ ውስጥ አይፈቀዱም - ኮምፖስቱን ያበላሻሉ።

ያከማቹት

የምግብ ትርፍራፊዎችን ለማከማቸት ጥብቅ-ክዳን ያለውን መያዣ ይጠቀሙ። በውስጡ የተጠራቀሙትን በምግብና የጓሮ ጥራጊ ማከማቻ ቅርጫት ውስጥ ይገልብጡ ፡ ከዚያም መያዣውን አለቅልቀው እንደገና ይጠቀሙበት።

ጋዜጣውን ይጠቀሙበት

የተዝረከረኩ የምግብ ትርፍራፊዎችን በጋዜጣው ጠቅለው ሁሉንም በቅርጫቱ ውስጥ ያከማቹ።

ያቀዝቅዙት

የምግብ ትርፍራፊዎችን በኮሮጆ ያድርጉ ወይም ይጠቅልሉ። ከዚያም ወደ ቅርጫት ውስጥ እስኪከማቹ ድረስ በማቀዝቀዣ ውስጥ ወይም ፍሪዘር ውስጥ ያስቀምጡ።

ይሸፍኑት

በቅርጫትዎ ውስጥ ፡ የምግብ ትርፍራፊዎችን ምግብ-በኑካካው ወረቀት ፡ በተቆራረጠ ወረቀት ፡ በእርጥብ ጋዜጣ ፡ ወይም በጓሮ ጥራጊ ይሸፍኑ።

የተፈቀደ ኮፖስታብል (ወደ አፈር ተለዋጭ) ኮሮጆ መሸፈኛ

For interpretation services please call 206-684-3000
ለቃል አስተርጓሚ አገልግሎት እባክዎን 206-684-3000 ይደውሉ
សូមទូរស័ព្ទមកលេខ 206-684-3000
如需口譯服務，請致電 206-684-3000
通訳のサービスが必要な場合は、206-684-3000までご連絡ください。
통역 서비스가 필요한 경우 206-684-3000번으로 전화하십시오.
สำหรับการบริการด้านการแปลภาษาระหว่างโทรศัพท์ 206-684-3000
Tajajila Turjjumanatiif 206-684-3000 bilbbila
Чтобы получить услуги переводчика, позвоните, пожалуйста, по телефону 206-684-3000
Adeegyada tarjumadda fadlan wac 206-684-3000
Para servicios de interpretación, por favor, llame al 206-684-3000
Para sa mga serbisyo ng pag-i-interpret, pakitawagan ang 206-684-3000
สำหรับบริการล่าม โปรดติดต่อ 206-684-3000
ናይ ምስተርጓም አገልግሎት እንተ ደሊኹም ብኸብረትኩም ኣብ 206-684-3000 ደውሉ።
Để có dịch vụ thông dịch, xin gọi số 206-684-3000

Seattle Public Utilities | Seattle Climate Action NOW | WM Waste Management Think Green. | cleanScapes BeyondWaste™